# ዓለምአቀፍ ማኅበረ እንባጠባቂዮች

## ግብረገብ

### መቅደም

የላቀ ፡ የእንባጠባቂ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ዓለምአቀፍ ፡ ማኅበረ ፡ እንባጠባቂዮች ፡ ቃል ፡ ገብቷል ። የዓለምአቀፍ ፡ ማኅበረ ፡ እንባጠባቂዮች ፡ የግብረገብ ፡ ደንብ ፡ በድርጅታዊ ፡ እንባጠባቂ ፡ ሥራቸው ፡ አባላት ፡ የሚገዙለት ፡ ፩ ፡ ወጥ ፡ ሙያዊ ፡ የግብረገብ ፡ አመለካከት ፡ ለማሠራጨት ፡ ሞኩራል ።

በእንባጠባቂ ፡ ሥራ ፡ ትውፊትና ፡ ሥነሥርዐት ፡ ተመስርቶ ፡ ይህ ፡ የግብረገብ ፡ ደንብ ፡ የሚያንጸባርቆ ፡ ታማኝነት ፡ ለግብረገባዊ ፡ ተግባር ፡ በእንባጠባቂ ፡ ሥራና ፡ የሙያው ፡ ቅንነት ፡ ለመጠበቅ ፡ ነው ።

የእንባጠባቂዮች ፡ ሐቀኞች ፡ መሆን ፡ አለባችውና ፡ በቅንነት ፡ መሥራት ፡ አለባቸው ። ለድርጅታቸው ፡ አባላት ፡ ሁሉ ፡ መከባበርን ፡ ማፍራት ፡ አለባችው ። በድርጅታችው ፡ ልማዶች ፡ ሂደቶችና ፡ ሕግጋተ ፡ አስተዳደርና ፡ አሠራር ፡ ፍትሐዊ ፡ ሥርዐት ፡ ማስፋፋት ፡ አለባችው ።

### ፬ቱ የግብረገብ ታላላቅ ቃላት

#### ግዕዝነት (ነጻነት)

በተቻለ ፡ መጠን ፡ በድርጅታቸው ፡ ውስጥ ፡ የእንባጠባቂዮች ፡ በመዋቅር ፡ በጥቅምና ፡ በእይታ ፡ ግዕዝነት ፡ አላቸው ።

#### አለማዳላት

ማዳላት ፡ ስለማይፈቀድላቸው ፡ በድርጅታቸው ፡ ውስጥ ፡ የእንባጠባቂዮች ፡ ገለልተኛና ፡ ወገን ፡ የለሽ ፡ ሰዎች ፡ መሆን ፡ አለባችው ። ጥርጣሬ ፡ ባለበት ፡ ሁኔታ ፡ አይሳተፉም ።

#### የምሥጢር ጥብቃ

የእንባጠባቂዮች ፡ ከእርዳታ ፡ የሚፈልጉ ፡ እንግዶች ፡ ጋር ፡ የሚያካሄዱት ፡ ንግግሮች ፡ ሁሉ ፡ አጥብቆ ፡ እንደማይለቅ ፡ ምሥጢር ፡ ይቆጥራሉና ፡ ያለ ፡ እንግዶቹ ፡ ፈቃድ ፡ ምሥጢሩን ፡ አይለቁትም ። ይኽንን ፡ ሕግ ፡ ለመጣስ ፡ የሚፈቀደው ፡ ከባድና ፡ ምራቅ ፡ የሚያስውጥ ፡ ጉዳት ፡ ለ፩ ፡ ሰው ፡ መድረሱ ፡ የማይቀር ፡ ከሆነ ፡ ከአረጋገጡ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

#### ኢመደበኝነት (ፈታ ያለ ዘዴና መላ)

ኢመደበኞች ፡ በመሆናቸው ፡ የእንባጠባቂዮች ፡ ስለተቀረቡላቸው ፡ ጉዳዮች ፡ በመደበኛ ፡ ድርጅታዊ ፡ ወይም ፡ መንግሥታዊ ፡ ዳኝነት ፡ ፍርድና ፡ ሥርዐተ ፡ አስተዳደር ፡ ሱታፌ ፡ የላቸውም።

www.ombudsassociation.org